# የኢሮብ ቋንቋና ባህል ማህበር የመጀመርያ ጉባኤ ዘገባ

## መግቢያ

ላለፉት ረጅም ዘመናት እየተፈራረቁብን የቆዩት ኢ-ዴሞክራስያዊ ሥርዓቶች በመላዋ ኢትዮጵያ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በማፈንና የዜጎችን መብት በመርገጥ በሥልጣን ኮረቻ ላይ ተንቀባርረው በመቀመጥ የአገዛዝ ዘመናቸውን እንዳሳለፉ የሚዘነጋ አይደለም። ለአገዛዛቸው እንዲያመቻቸውም ብሔር ብሔረ-ሰቦችን እያለያዩ እርስ በርስ በማጣላት፣ ቋንቋና ባህላቸውን እንዳያሳድጉና እንዳያበለጽጉ በመከልከል፣ በገዛ አገራቸው ውስጥ እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንዲቆጠሩ ሲያደርጉዋቸው እንደነበረ የቅርብ ጊዜ የማይረሳ ትዝታችን ነው። ይህ በእንዲህ እያለ የህዝቦች ጭቆና እንደዚህ መቀጠል እንደሌለበት በወቅቱ የተገነዘቡና ይህን ጭቆና ለማስወገድ መታገል የግድ መሆኑን ያመኑና ኢ-ፍትሀዊ ቀንበርን ተሸክሞ ከመኖር ይልቅ ህይወታቸውን በመሰዋት ለቀጣይ ትውልድ የተሻለች አገር ማውረስ ይሻላል ብለው ለተነሱትና ለወደቁት የህዝብ ልጆች ምስጋና ይደረሳቸውና ዛሬ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሕግ መንግስት ውስጥ ተካትተው መራመድ ጀምረዋል።

ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ አስታዋሽ አጥተው ከቆዮት ቋንቋዎችና ባህሎች የኢሮብ ብሄረሰብ ቋንቋና ባህል አንዱ ነው። በርግጥ በደርግ አገዛዝ ዘመን የተለያዩ የኢሮብ ቋንቋ ጥናትና ምርምር ሙከራዎች ተደርገዋል። ሆኖም ግን እነዚህ ጥናቶችና ምርምሮች ተጨባጭ ውጤት ያስገኙ አልነበሩም። ምክንያቱም፤ ይካሄዱ የነበሩ ጥናቶችና ምርምሮች የኢሮብ ህዝብ ቋንቋና ባህልን ማእከል ያደረጉ ስላልነበሩ፣ ከብሄረሰቡ ውስጥ ባህሉንና ቋንቋውን በሚገባ የሚያውቁ ያሳተፉ ስላልነበሩ፣ እንዲሁም ደግሞ ቋንቋ የአንድ ህዝብ ባህላዊ እሴቶች መግለጫ እንደመሆኑ መጠን፣ ጥናቶቹ ይህንን ያላካተቱ ስላልነበሩ ነው።

የደርግ አገዛዝ ተወግዶ የኢህአደግ መንግስት ሥልጣን ከያዘ በኋላ ለብሄር ብሄረሰቦች መብት ትኩረት ሰጥቶ ማንኛውም ብሄርና ብሄረሰብ የራሱ ቋንቋና ባህል ለማሳደግ በሩን ከፍቷል። በዚህ ኢሮብም እንደ ሌሎች ብሄረሰቦች የራሱ ቋንቋ (ሳሆ) በማሳደግ ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ለማድረግ ተችሏል፣ በ2000 ዓ.ም የሳሆ የቋንቋ ጥናት ተደርጎ ህዝባችን ከወረዳ እስከ ውጭ አገር ነዋሪ የተሳተፈበት ጉባኤ ከጳጉሜን 1-2/2000 ዓ.ም በዳውሃን ከተማ ተካሂዶ የኢሮብ ቋንቋ የሚጻፍበት ፊደል ግእዝ ይሁን ወይስ ላቲን በሚለው ሰፊ ውይይት ተካሂዶ **የግዕዝ ፊደል** እንዲሆን በሙሉ ድምፅ በስምምነት ተወስኗል። ይህ ውሳኔ በተጠቀሰው ጉባኤ ከፀደቀ በኋላ ሕጋዊ እንዲሆን የኢሮብ ወረዳ ምክር ቤት ማፅደቅ ስለነበረበት፤ በጥቅምት 29/2001 ዓ.ም ለምክር ቤቱ ቀርቦ ምክርቤቱ የተደረገው ጥናት በጣም ጥሩና በቀጣይነት በማካሄድ ሊጠናከር የሚገባው መሆኑን በማስገንዘብ ያለምንም ተቃውሞ የጉባኤውን ውሳኔ እንዳለ ተቀብሎ አጽድቆታል። የኢሮብ ቋንቋ መፃፊያም **የግዕዝ** ፊደል እንድሆን በሙሉ ድምፅ ወስኖዋል።

የኢሮብ ቋንቋ ጥናት ቢጀመርም ገና በጣም ብዙ እንደሚቀረው ለሁላችንም ግልጽ ነው። የኢሮብ ቋንቋ ጥናት አስተባባሪ ኮሚቴ የነበረው አካል፤ እንደ አጀማመሩ የጥናት ኮሚቴ ሆኖ ከመቀጠል ይልቅ ከብሂረሰቡ መሳተፍ የሚፈልጉትን የሚያሳትፍ በማህበር ደረጃ ተደራጅቶ ለመስራት መቻል የኢሮብ ቋንቋና ባህል እንድያድግና ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ወሳኝ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ስለታመነበት፤ መስከረም 27/2001 ዓ.ም ከትግራይ ፍትሕ ቢሮ በተሰጠው ፍቃድ መሰረት የኢሮብ ቋንቋና ባህል ማህበር ለመመሰረት ችሏል።

## የኢሮብ ቋንቋና ባህል ማህበር ከተመሰረተ በኋላ የተሰሩ ሥራዎች

1. የወረዳው ምክር ቤት ያፀደቀውን ውሳኔ ለሚመለከታቸው የመንግስትና የግል ድርጅቶች ከምክር ቤቱ በተፃፈ ደብዳቤ መሰረት እንድያውቁት አሰተባብሮዋል።
2. ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩና የቋንቋ ባለሙያ በክልል ትምህርት ቢሮ እንዲመደብልን ለክልል አሰተዳደር ጥያቄ በማቅረብ መንግስት ለጠየቅነው ጥያቄ በአፍጣኝ ምላሽ ሰጥቶናል።
3. በ1ኛ ክፍል የተጀመረው የሳሆ ቋንቋ ትምህርት አካሄድ ለመገምገም ሰኔ 2002 ዓ.ም ከ8 ትምህርት ቤቶቾ ከተውጣጡ ተማሪዎች ጋር የጥያቄና መልስ ውድድር በማካሄድ የሳሆ ቋንቋ ትምህርት በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን ከመገንዘቡ በተጨማሪ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ለወጡ ተማሪዎች ሽልማት ሰጥቷል።
4. ከሁሉም የወረዳው ዕሕፈት ቤቶች ከተውጣጡ የኢሮብ ተወላጆችና የሳሆ የቋንቋ ባለሙያ (ቴክንካል) ኮሚቴ አባሎች ጋር በመሆን የሳሆ ቋንቋ ራሱን የቻለ ስታንዳርድ ያለው ዕሑፍ እንዲኖረው የሚያስችል ጥናት በ2002 ዓ.ም በመቀሌ ከተማ አካሂዷል።
5. የኢሮብ ተወላጅ የኪነት ሰዎች ያስቀረጿቸው የጥበብ ውጤቶች ባስተዋወቁባቸው ጊዜያት በሃሳብ፣ በገንዘብ እንዲሁም በምረቃ ወቅት ለምረቃ የሚሆን መሰብሰብያ አዳራሽ በማዘጋጀትና የምረቃ ፕሮግራም በመምራት የኢሮብ ባህል እንዲያድግ ጥረት አድርጓል።

## የኢሮብ ቋንቋና ባህል ማህበር የመጀመርያ ጉባኤ

የኢሮብ ቋንቋና ባህል ማህበር የመጀመርያ ጉባኤ ሓምሌ 10 ቀን 2003 ዓ.ም ከኢሮብ ወረዳ ሰባት ቀበሌዎች፤ የመንግስት ዕሕፈት ቤቶች፣ ከመቀሌና ከዓዲግራት የተወከሉ የኢሮብ ተወላጆች የተሳተፈውበት በዓድግራት ከተማ በደማቅ ሁኔታ ተካሂዶዋል።

## የጉባኤው ዋና ዋና አጀንዳዎች

1. የማህበሩ ያለፈውን እንቅስቃሴ የሚዳስስ ሪፖርት ማቅረብ፤
2. የኢሮብ ቋንቋና ባህል ማህበር (Irob Language & Cultural Association) (ILCA) መተዳደሪያ ደምብ ማጽደቅ፤
3. ቀጣይ የማህበሩ የ4 ዓመት የሥራ እቅድ ማጽደቅ፣
4. የማህበሩ የውስጥ ኦዲተር መምረጥ፤
5. ለአራት አመት ማህበሩን በበላይነት የሚመራ አመራር መምረጥ፣

## በጉባኤው የተወሰኑ ውሳኔዎች

1. የማህበሩ ቦርድ አባላት 9 እንዲሆኑ ተወስነዋል።
2. የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን 4ት ዓመት እንዲሆን ተወሰኖዋል።
3. የማህበሩ ዋና ፅሕፈት ቤት ለጊዜው በመቀሌ ከተማ እንዲሆን ተወስነዋል።
4. የኢሮብ ቋንቋ እንድታቀብ እስካሁን ድረስ የተደረገ ጥረት እጅግ የሚደነቅ ነው::

ይህንን ስራ የሰሩት የኛ የኢሮብ ሙሁራን በመሆናቸውም ኩራት ይሰማናል:: ሆኖም ባህላችንንና ቋንቋችንን ከማስጠበቅና ከማሳደግ ሥራ ጎን ለጎን አከባቢያችንን የማልማት ከፍተኛ ሥራም ይጠብቀናል። ይሁን እንጂ ሁሉም ሥራዎች በአንድ ማኅበር ሊከናወን የማይችል፤ ዘርፈ ብዙ ስለሆነ ማኅበራችን ቋንቋና ባህላችን ላይ ትኩረት ለማድረግ ይገደዳል። በመሆኑም ጉባኤአችን ሁሉም የኢሮብ ተወላጅ ቋንቋችንና ባህላችንን በሚገባ ለማጠናከርና ለመጠበቅ በማተሪያል ሆነ በሃሳብ የቻለውን ሁሉ ድጋፉን በመለገስ ማህበሩን ለማጠናከርና ለማሳደግ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ጥሪ በማቅረብ ይህ ማኅበር ለቋንቋና ለባህል እድገት ብቻ ልዩ ትኩረት በመስጠት እንዲንቀሳቀስ ሲል በሙሉ ድምፅ ወስነዋል።

## የቦርደ አባላትና ኦዲተር ምርጫ

**ኦዲተር፣-** የማህበሩ ዋና ኦዲተር አቶ አድሓኖም መድኅን ፋሡሕ እንዲሆን በሙሉ ደምፅ ተመርጠዋል።

**የአመራር ቦርድ አባላት**

| ተ.ቁ. | ሙሉ ስም | ኃላፊነት | አድራሻ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ዶሪ አስገዶም | ቦርድ ዳይሬክተር | መቀሌ |
| 2 | አቶ ሉሉፍ ዓሳዓሊ | ም/ቦርድ ዳይሬክተር | መቀሌ |
| 3 | አቶ አለማ ገብራይ | ቦርድ ፀሓፊ | መቀሌ |
| 4 | መም/ር ፍሱሕ ገብራይ | አባል | ዳውሃን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | መም/ር ግርማይ ፍሱሕ | አባል ´ | ዓዲግራት |
| 6 | መም/ር ሃ/ስላሴ ተሰፋይ | አባል | ዓዲግራት |
| 7 | ኣይተ ሃውኩ ረዳኩም | አበል | ዓዲግራት |
| 8 | ወ/ሪት ትብለፅ ካሕሳይ | አባል | መቀሌ |
| 9 | አቶ አምሃ ዮሃንስ | አባል | መቀሌ |

**<u>ማሳሰቢያ</u>**

ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም በተፈለገው መጠንና ፍጥነት በስራ ላይ ውለው
የብሄረሰቡ ተወላጆቿ በቋንቋቸውና በባህላቸው ኮርተው፤ መጪው ትውልድ በተሻለ መሰረት ላይ የቆመና ለቋንቋውና ለባህሉ የሚቆረቆር ለማድረግ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ያሉት የኢሮብ ተወላጆቹና ወዳጆቹ ሁሉ ይህንን ማህበር በገንዘብ፣ በንብረትና በእውቀት እንዲረዱና ለዚህ በጎ ተግባር እጃቸውን ዘርግተው ቋንቋችንንና ባህላችንን እንዲታደጉትና እንዲያሳድጉት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ከሰላምታ ጋር

የኢሮብ ቋንቋና ባህል ማህበር የስራ አመራር ቦርድ

ሐምሌ 2003 ዓ.ም

**ከማኅበራችን ጋር ለመገናኘት የሚከተሉትን አድራሻዎች ይጠቀሙ**

1. doriasgedom@yahoo.com
2. silassie77@gmail.com